
# አካባቢ ሳይንስ



## መማሪያ መጽሐፍ

## አንደኛ ክፍል

# አካባቢ ሳይንስ

## መማሪያ መጽሐፍ

## አንደኛ ክፍል

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ት/ቢሮ

## በደብረ ብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የተዘጋጀ


**አዘጋጆች፡-**

1. ሲሳይ ሀይሉ
2. በለጠ ከበደ
3. ነቅንቄ ዘውዴ
4. አሰፋ ይሁኔ
5. ዘነበ ሽፈራው

**አርታኢዎች፡-**

1. በለጠ አየለ
2. በቀለ ደጉ
3. አሊ ሀሰን
4. አብዱራህማን ይማም
5. ወሰን አያሌው

**ዋና አርታኢዎች፡-**

1. መልኬ ክፍሌ
2. ህብስቴ ካሴ
3. ሙሉጌታ መሥፍን

ሰዓሊ፡- በላይሁን ፀጋዬ

© አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ፣ 2004

# <u>ምስጋና</u>

ይህንን የአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መጽሐፍ እንድናዘጋጅ ሁኔታዎችን ላመቻቸልን የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮና እንዲሁም ሁልጊዜ ከጎናችን በመሆን ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልን ለአቶ ማሙዬ ገብረሕይወት የደብረብርሃን መምህራን ትምህርትና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ዲን ከፍ ያለ ምሥጋና እናቀርባለን፡፡ በተጨማሪም የኮምፒውተር ትየባውን በጥራትና በቅልጥፋና ላከናወኑልን ለወ/ሮ አይናለም ሲሳይ እና ለወ/ሮ ምስራቅ ግርማ ምሥጋና እናቀርባለን፡፡

# መግቢያ

ይህ የአንደኛ ክፍል  የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት መማሪያ መፅሐፍ በአዲሱ መርሀ ትምህርት  ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ነው፡፡ መፅሐፉ የአካባቢን ነባራዊ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡ አራት ምዕራፎችን አካቷል፡፡ እነዚህም ሰውና ኑሮው፣ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤታችን እና አካባቢያችንና ቀበሌያችን የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም መምህራን የሕፃናቱን አካላዊና ሥነ  አዕምሯዊ ዕድገት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ  የሚጠበቁትን የባህርይ ለውጦች ለማምጣት ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

አዘጋጆቹ

# ማውጫ

ርዕስ
ገፅ
መግቢያ
ምዕራፍ አንድ፡- ሰውና ኑሮው

1.1 የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

1

1.2 መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን

6

1.3 ሰውን አዘውትረው የሚያጠቁ በሽታዎች

10

1.4 አምስቱ አባላተ ስሜቶች

13

ምዕራፍ ሁለት፡-ቤተሰብ

2.1 የቤተሰብ አባላት

19

2.2 የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶች

23

2.3 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሣቁሶች

34

ምዕራፍ ሶስት፡-ትምህርት ቤታችን

3.1 የትምህርት ቤታችን ግቢ

46

3.2 ደንብና ስነ-ስርዓት ማክበር 51

3.3 መልካም ግንኙነትን መመስረት 52

3.4 የመንገድ ላይ ትራፊክ ደህንነት 54

3.5 በትምህርት ቤታችን ውስጥ ከወረቀት የምንሰራቸው መጫወቻዎች 57

ምዕራፍ አራት፡-አካባቢያችንና ቀበሌያችን

4.1 አቅጣጫን ማወቅ 58

4.2 በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት የሌላቸው ነገሮች 62

4.3 በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች 69

4.4 በአካባቢያችን የተለመዱ የሥራ አይነቶች 87


4.5. የአካባቢያችን መጓጓዣ 91

# ምዕራፍ አንድ

# ሰውና ኑሮው

## 1.1. የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

### 1.1.1. የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን መለየት




**ሥዕል 1.1** *የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች*

**መልመጃ፡** 1.1.

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን በመንካት ስማቸውን አጠገባችሁ ላሉ ተማሪዎች ተናገሩ።
2. ከዚህ በላይ ያለውን የሰው ሥዕል በመመልከት በቁጥር የተመለከቱትን የሰውነት ክፍሎች ሥም ተናገሩ።

**መልመጃ፡** 1.2.

1. ጭቃ ወይም ወረቀት ወይም ጨርቅ ተጠቅማችሁ፣ የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን የሚያሣይ አሻንጉሊት ሥሩ፡፡
2. የሰራችሁትን አሻንጉሊት እንዴት እንደሰራችሁት ተናገሩ፡፡
3. አሻንጉሊቱ ምን ምን የሰውነት ክፍሎችን እንደያዘ ተናገሩ፡፡


### 1.1.2. የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራት

**መልመጃ፡**1.3

1. ጆሮ ለምን ይጠቅማል?
2. ዓይን ለምን ይጠቅማል?
3. እግር ለምን ይጠቅማል?


## የሰውነት ክፍሎችን ጥቅም መናገር












ሥዕል 1.2 *የሰው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራት*

**መልመጃ 1.4**

1. የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻችሁን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን አከናውኑ፡፡ **ምሳሌ** መራመድ፣ መሮጥ፣ መዝለል፣ማሽተት፣ ማየት፣ መፃፍ፣ የእንስሳት ወይም የከበሮ ድምፅ መስማት፣ ኳስ መጫወት…
2. ከላይ ያከናወናችኋቸውን ተግባራት ለመስራት የተጠቀማችሁበትን የሰውነት ክፍል ተናገሩ፡፡

### 1.1.3. ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ ማድረግ



ሥዕል 1.3 *ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ ማድረግ*

**መልመጃ 1.5**

1. እጅን መታጠብ ለምን ይጠቅማል?
2. ፊትን መታጠብ ለምን ይጠቅማል?
3. እግርን መታጠብ ለምን ይጠቅማል?
4. ፀጉርን መታጠብና ማበጠር ለምን ይጠቅማል?
5. ጥርስን መፋቅ፣ እና ጥፍርን መቁረጥ ለምን ይጠቅማል?
6. ከላይ ያሉትን ሥዕሎች በመመልከት ሰዎች ምን እያደረጉ እንደሆነ ተናገሩ፡፡


## 1.2 መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን

### 1.2.1 የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች

ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በትኩረት ተመልከቱና ለጥያቄዎቹ መልስ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**መልመጃ 1.6**


1. ሥዕል 1.4 ላይ ምን ተመለከታችሁ?
2. ሥዕል 1.5 ላይ ምን ተመለከታችሁ?
3. ሥዕል 1.6 ላይ ምን ተመለከታችሁ?



ሥዕል 1.4 የምግብ ዓይነቶች



ሥዕል1.5 ልብሶች





ሥዕል 1.6 መጠለያዎች

**መልመጃ 1.7**

የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉት ሦስቱ መሰረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን ናቸው? ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ለመኖር የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-**ምግብ ፣ ልብስና መጠለያ** ናቸው፡፡ እነዚህም የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ይባላሉ፡፡

## 1.2.2 የመሠረታዊ ፍላጐቶች አስፈላጊነት

**መልመጃ 1.8**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመምህራችሁ ተናገሩ

1. ምግብ መመገብ ለምን ያስፈልጋል?
2. ልብስ ለምን ትለብሳላችሁ?
3. የመጠለያ ጥቅም ምንድን ነው ?



ሥዕል 1.7 የመሠረታዊ ፍላጎቶች አስፈላጊነት

## 1.3. ሰውን አዘውትረው የሚያጠቁ በሽታዎች

### 1.3.1. የተለመዱ በሽታዎች

**መልመጃ** 1.9

1. ታማችሁ ታውቃላችሁ?
2. ምን ምን በሽታዎችን ታውቃላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ በብዛት ሰዎችን የሚያጠቁ እና የተለመዱ በሽታዎች ስም ዘርዝሩ::

### 1.3.2. ኤድስ

**መልመጃ** 1.10

1. ከአሁን በፊት ስለ ኤድስ በሽታ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. የኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡

### 1.3.3. በሽታን መከላከል

**መልመጃ** 1.11

1. ከጉንፋን በሽታ ራሳችንን እንዴት እንከላከላለን ?
2. ከተቅማጥ በሽታ ራሳችንን እንዴት እንከላከላለን ?
3. ከወባ በሽታ ራሳችንን እንዴት እንከላከላለን ?
4. ከኤድስ በሽታ ራሳችንን እንዴት እንከላከላለን ?





ሥዕል 1.8 *በሽታ በትንፋሽ የሚተላለፍበት መንገድ*



ሥዕል 1.9 *በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታን መከላከያ መንገድ*



*ሥዕል* 1.10 *በሽታ በዝንብ ይተላለፋል*

**መልመጃ**1.12

1. ሁል ጊዜ ከመጸዳጃ ቤት ስትመለሱ እጅን መታጠብ ለምን ይጠቅማል?
2. በቆላማ አካባቢ በአጎበር /በዛንዚራ/ ውስጥ መተኛት ለምን ይጠቅማል?

## 1.4. አምስቱ አባላተ ስሜቶች

### 1.4.1. የአባላተ ስሜቶች ስም



ምላስ



ዓይን



ጆሮ



እጅ



አፍንጫ

*ሥዕል* 1.11 *አምስቱ አባላተ ስሜቶች*

## 1.4.2. የአባላተ ስሜቶች ተግባራት

**መልመጃ** 1.13

1. የዓይንን ተግባር ግለጹ፡፡
2. የጆሮ ተግባር ምንድን ነው?
3. የአፍንጫን ተግባር ግለጹ፡፡
4. የነገሮችን ሻካራነትና ለስላሳነት እንዴት መለየት ይቻላል?
5. ስኳር ጣፋጭ መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻላል?
6. የምትመገቡት ምግብ ጨው ያለበት መሆኑ እንዴት ታውቃላችሁ?




*ሥዕል* 1.12 *ዓይን እና የብርሃን ምንጮች*

## ቀለማትን መለየት


**መልመጃ 1.14**

1. ዛፎች ምን ዓይነት ቀለም አላቸው?
2. የለበሳችኋቸው ልብሶች ምን ዓይነት ቀለማት አሏቸው?
3. በሰንደቅ ዓላማ ስነ-ስርዓት የሚሰቀለውን ባንዲራ ቀለማትን ለዩ፡፡



ሥዕል 1.13 ቀስተ ዳመና ቀለማት

**የተለያዩ ድምፆችን ለመስማት**




*ሥዕል* 1.14 *የጆሮ ጥቅም*



*ሥዕል* 1.15 *የአፍንጫ ጥቅም*



## ጣፋጭነት፣ መራራነትና ጨዋማነትን መለየት

*ሥዕል* 1.16 *የምላስ ጥቅም*



ቀዝቃዛነትንና  ሙቅን መለየት    ለስላሳነትንና ሻካራነትን መለየት

*ሥዕል* 1.17 *የእጅ ጥቅም*

# ምዕራፍ ሁለት

# ቤተሰብ

## 2.1. የቤተሰብ አባላት



የወይዘሮ አቻምየለሽ ቤተሰብ



የአቶ አለሙ ቤተሰብ

*ሥዕል* 2.1 *የቤተሰብ አባላት*

### 2.1.1. የቤተሰብ አባላት ዝርዝር

ተማሪዎች ! በሥዕሉ ውስጥ ያሉትን የቤተሰብ አባላት ለዩ፡፡

የቤተሰብ አባላት በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡ እነሱም አባት፣ እናት፣ ወንድም እና እህት ናቸው፡፡ በተጨማሪም አያት፣ አጎት፣ አክስት እና ሌሎችም ሰዎች አብረው ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የእናንተን ቤተሰብ አባላት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### 2.1.2 የቤተሰብ አባላት በመከባበርና በመረዳዳት መኖር




*ሥዕል* 2.2 *የቤተሰብ አባላት ሲረዳዱ*

የቤተሰብ አባላት በመከባበር፣ በመመካከርና በመደጋገፍ አብረው መኖር ያለባቸው ለምን ይመስላችኋል?

## 2.1.3. የቤተሰብ መተዳደሪያ ሥራ


ተማሪዎች! የወላጆቻችሁን መተዳደሪያ ሥራዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ ፡፡



ግብርና



ሽመና




መምህርነት



ምህንድስና



አናጢነት




ህክምና

*ሥዕል 2.3 የቤተሰብ የተለያዩ መተዳደሪያ ሥራዎች*


ተማሪዎች ሌሎች የቤተሰብ መተዳደሪያ ሥራዎች ታውቃላችሁ? እስቲ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

የቤተሰብ መተዳደሪያ ሥራ ለቤተሰብ ምን ጠቀሜታ አለው?

## 2.1.4. ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ተከባብሮ መኖር



ሽማግሌዎች በሰፈር ውስጥ በጋራ ሲወያዩ፡፡



ልጆች በሰፈር ውስጥ ተከባብረው በጋራ ይጫወታሉ፡፡

*ሥዕል* 2.4 *በጋራ ተከባብሮ መኖር*

## 2.2. የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶች

- *ተማሪዎች*! በምዕራፍ አንድ የሰው ልጅ *መሠረታዊ* ፍላጎቶችን *ተምራችኋል*፡፡ ከተማረችሁት ምን ታስታውሳላችሁ? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
- የቤተሰብም *መሠረታዊ* ፍላጎቶች *ሦ*ስት ናቸው፡፡ እነርሱም ምግብ፣ መጠለያና ልብስ ናቸው፡፡

### 2.2.1. ምግብ

እስቲ ተማሪዎች ቀጥሎ ያለውን መዝሙር ከመምህራችሁ ጋር ዘምሩ፡፡

**መዝሙር**

ምግብ ለጤናችን፣
ምግብ ለእድገታችን፣
ምግብ የጉልበት ምንጫችን፣
ምግብ የመኖር ዋስትናችን፡፡ /2/

ተማሪዎች ከመዝሙሩ ምን ተረዳችሁ?

ከመዝሙሩ እንደተረዳችሁት ምግብ በሕይወት ለመኖር አስፈላጊ ነው፡፡



*ሥዕል* 2.5 *የተለያዩ ምግቦች*

## ሀ. የምግብ ምንጮች

መልመጃ 2.1

1. ከዕጽዋት የሚገኙ ምግቦችን ዘርዝሩ፡፡
2. ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦችን ዘርዝሩ፡፡

ምግብን የምናገኘው ከግብርና ሥራ ከሚገኙ ምርቶች ነው፡፡



ሥዕል 2.6 የግብርና ሥራ

## ለ. የተለመዱ እህሎች

**መልመጃ 2.2**

1. አርሶ አደሮች ምን  ምን ያመርታሉ?
2. የግብርና ሙያ የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

አርሶ አደሮች ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ ሰብሎችን ያመርታሉ፡፡ ሙያውም ግብርና ይባላል፡፡ተማሪዎች! ወላጆቻችሁን በመጠየቅ በአካባቢያችሁ የሚመረቱ ሰብሎችን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡


## ሐ. የእህል ውጤቶች



ዳቦ



ብስኩት



እንጀራ



ዘይት



ፓስታ



ማካሮኒ

*ሥዕል 2.7 የእህል ውጤቶች*

ከላይ በሥዕሉ የተመለከቱት ምግቦች ከየትኛው የእህል ዘር እንደተገኙ ግለፁ፡፡

## 2.2.2. ልብስ

### ሀ. የልብስ አይነቶች


**መልመጃ** 2.3

1. ተማሪዎች! ባህላዊና ዘመናዊ ልብሶች ታውቃላችሁ?
2. ቤተሰቦቻችሁ ባህላዊና ዘመናዊ ልብሶችን መቼ መቼ ይለብሳሉ?


ልብስ አካላችንን ለመሸፈን ይጠቅመናል፡፡ ልብስ ከብርድ፣ ከዝናብ፣ ከኃይለኛ የፀሐይ ብርሃንና ከአደጋ ይጠብቀናል፡፡



ቀሚስ



ጋቢ



ቆብ

ባህላዊ ልብሶች




**ጃኬት**



**ቀሚስ**



**ሱሪ**



**ሸሚዝ**



**ኮት**

**ዘመናዊ ልብሶች**

*ሥዕል* 2.8 *የልብስ አይነቶች*

**ሰዎች እንደየአካባቢው ባህልና የአየር ጠባይ ሁኔታ የተለያዩ ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ፡፡ ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ለተለያዩ ሁኔታዎች የሚለበሱ የልብስ አይነቶችን ቀጥሎ በተመለከተው ሰንጠረዥ ውስጥ አሟሉ፡፡**

ሠንጠረዥ 2/1 በተለየዩ ሁኔታዎች የሚለበሱ ልብሶች

| ሁኔታ | የሚለበሱ የልብስ ዓይነት |
|---|---|
| ዝናብ | |
| ፀሐያማ | ስስ፣ ነጭና ቀላል |
| ብርድ | |
| ግብዣ | ዘመናዊ ሙሉ ልብስ |
| በዓል | |

## ለ. ልብስ ለመስራት የሚያገለግሉ ነገሮች


**መልመጃ** 2.4

1. ልብስ ለመስራት የሚያገለግሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. ልብስ ለመስራት የሚያገለግሉ ነገሮች ከየት ይገኛሉ?

ተማሪዎች! የምንለብሳቸው ልብሶች ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ከሐር፣ ከቆዳ፡ ከናይለንና ከሌሎች ነገሮች ሊሠሩ ይችላሉ፡፡



ከቆዳ የተሰሩ አልባሳት

ከጥጥ የተሰሩ አልባሳት





ከሱፍ የተሰሩ አልባሳት

ከሐር የተሰሩ አልባሳት

*ሥዕል 2.9 ከተለያዩ ነገሮች የተሠሩ አልባሳት*

**መልመጃ 2.5**

ቀጥሎ ለተመለከቱት ጥያቄዎች ከላይ ሥዕሉን በመመልከት ምላሽ ስጡ፡፡

1. ከጥጥ የሚሠሩ አልባሳትን ዘርዝሩ፡፡
2. ከቆዳ ምን ምን አልባሳት ሊሠሩ ይችላሉ?
3. ከሱፍስ ምን አይነት አልባሳት ሊዘጋጁ ይችላሉ?
4. ከናይለን የሚሠሩ አልባሳትን ዘርዝሩ፡፡

አልባሳት ከተለያዩ ነገሮች የሚሠሩት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

- ለጥንካሬ
- ለሙቀት
- ለውበትና
- ቀለል ያሉ እንዲሆኑ ሲፈለግ ነው፡፡

### 2.2.3 መጠለያ

### ሀ. የመጠለያ አይነቶች

**መልመጃ 2.6**

1. መጠለያ ማለት ምን ማለት ነው?
2. መጠለያ ለምን ያገለግለናል?
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የመጠለያ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

የምንኖርበት ወይም ስራ የምንሰራበት ቤት መጠለያ ይባላል፡፡ ሰዎች ለቤት እንስሳትም መጠለያ ይሰራሉ፡፡ መጠለያ ከዝናብ፣ ከብርድ፣ ከውርጭ፣ከኃይለኛ የፀሐይ ብርሃንና ከመሳሰሉት አካባቢያዊ ሁኔታዎች እራሳችንን ለመጠበቅ ያገለግለናል፡፡እንዲሁም መጠለያ ንብረታችንን ለመጠበቅ፣ ለመማሪያና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ይጠቅመናል፡፡



*ሥዕል 2.10 ግቢው የታጠረ የሣር መኖሪያ ቤት*

**የመጠለያ ዓይነቶች ሣር ቤት ፣ ቆርቆሮ ቤት ፣ ሸክላ ቤት ወይም ፎቅ ቤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡**



**ሣር ቤት**



**ቆሮቆሮ ቤት**



**ሸክላ ቤት**



**ፎቅ ቤት**

*ሥዕል* 2.11 *የተለያዩ የመጠለያ አይነቶች*

| |
|---|
| **መልመጃ 2.7** |
| 1. መጠለያ ለመሥራት  የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶች ምን ምን ናቸው? |
| 2.  መጠለያ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶች ከየት ይገኛሉ? |

መጠለያ ለመስራት እንደ መጠለያው ዓይነት ጭቃ፣ ቆርቆሮ፣ ሣር፣ እንጨት፣ ብሎኬት፣ ሸክላ ጡብ፣ ድንጋይ ፣ ሲሚንቶ፣ የብረት ዘንጎች፣  ወዘተ ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ! በቡድን በመሆን እነዚህን መጠለያ ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን የሣር ቤት፣ የቆርቆሮ ቤት፣ የሸክላ ቤት፣ ህንፃ ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በማለት ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩዋቸው፡፡

## 2.3. የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሣቁሶች

### 2.3.1. የቤት ውስጥ ቁሣቁስ ዓይነቶች

| |
|---|
| **መልመጃ 2.8** |
| 1. የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ከምን ከምን የተሠሩ ይመስላችኋል? |
| 2. የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ምን ምን ጥቅም ይሰጡናል ? |


የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች የሚባሉት መቀመጫዎች፣ መመገቢያ ዕቃዎች፣ ሣጥን፤ እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ እቃዎች ናቸው፡፡

እስቲ አሁን የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች የሚሰጡትን ጥቅም እንመልከት፡፡

## ሀ. በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሣቁሶች

**መልመጃ 2.9**

በቤታችሁ ውስጥ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ቁሶቁሶች አሉ? ካሉ ምን ምን ጥቅም ይሰጧችኂል?




ሥጋና ፍራፍሬ የያዘ ማቀዝቀዣ



ልብስ በኤሌክትሪክ ካውያ ሲተኮሰ



ፀጉር የሚያስተካክል ሰው




ቴሌቪዥን የሚመለከቱ የቤተሰብ አባላት

*ሥዕል* 2.12 *በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች*



ሀ. የኤሌክትሪክ ምጣድ ላይ እንጀራ ሲጋገር




ለ. በኤሌክትሪክ ምድጃ  ላይ የተጣደ ውሃ


*ሥዕል* 2.13 *በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች*

**ተማሪዎች! ከላይ በስዕሉ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ቁሳቁሶች አሉን? እስቲ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።**

**ለ.ኤሌክትሪክ የማያስፈልጋቸው የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች**


ተማሪዎች! ከታች በስዕሉ ከሚታዩት በኤሌክትሪክ የሚሰራ አለን?





አልጋ


ጠረጴዛና ወንበር



መደርደሪያ



ጀበና



ብርጭቆ

*ሥዕል 2.14 ኤሌክትሪክ የማያስፈልጋቸው የቤት ውሰጥ ቁሣቁሶች*

**መልመጃ 2.10**

1. ከላይ በሥዕሉ የተመለከቱት ቁሣቁሶች ምን ምን ጥቅሞች ይሰጣሉ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. በየቤታችሁ ያሉትን ኤሌክትሪክ የማያስፈልጋቸውን የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ስም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ሐ. የማዕድ ቤት ቁሣቁሶች

መልመጃ 2.11

1. ተማሪዎች! በማዕድ ቤት ውስጥ ቤተሰቦቻችሁ የሚሠሯቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?
2. ቤተሰቦቻችሁ በማዕድ ቤት ውስጥ ምን ምን ቁሣቁሶችን ይጠቀማሉ?

እስቲ የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡




ሥዕል 2.15 *የማዕድ ቤት ቁሣቁሶች*

## 2.3.2 የቤት ውስጥ ቁሳቁሳች የሚሰጡት ጥቅም

### ሀ. በኤሌክትሪክ የሚሠሩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሣቁሶች

በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች ለመብራት፤ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመዝናኛ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ምሳሌ፡- ቴሌቪዥን፣ ሬድዮ፣እና ቴፕሪከርደር፡፡

### ለ. ኤሌክትሪክ የማያስፈልጋቸው ቁሳቁሳች

እንደ ወንበር፣ አልጋ፣ መደርደሪያ ጠረጴዛ የመሳሰሉት ደግሞ ለመቀመጫ፣ ለመኝታ፣ ለዕቃ ማስቀመጫና ለተለያዩ አገልግሎት ሊውሉ ይችላሉ፡፡

### ሐ. የማዕድ ቤት ቁሣቁሶች

ምግብ ለማዘጋጀት፤ለምሳሌ ብረት ድስት፤ ሸክላ ድስት፤ቢላዎች ወዘተ

### መ. በቤት ውስጥ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች


**መልመጃ 2.12**

1. ተማሪዎች! በቤት ውስጥ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ቁሣቁሶች ስም ተናገሩ፡፡
2. አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች አደጋ እንዳያስከትሉ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. የኤሌክትሪክና ስለታማ ዕቃዎችን በጥንቃቄ መጠቀም ለምን ያስፈልጋል?

ተማሪዎች! በኤሌክትሪክ ኃይል ወይም ጉልበት የሚሠሩ ቁሣቁሶች ለምሳሌ ማብሰያ ቁሣቁሶች፣ ካውያና የመሳሰሉት እንዲሁም ስለታማ የሆኑ ነገሮች በቀላሉ አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ቁሣቁሶች በጥንቃቄ መጠቀም ይገባናል፡፡




ካውያ




ምድጃ




ቢላዋ



ክብሪት



ቡታጋዝ



ሲልንደር

*ሥዕል* 2.16 *አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች*

### 2.3.3 የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ተማሪዎች! አሁን ደግሞ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶችን ለመሥራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን እንማራለን ። የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች ከተለያዩ ነገሮች ሊሠሩ እንደሚችሉ ከዚህ በፊት ተምራችኋል። አስቲ የምታስታውሱቱን በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ሙሉ።

**ሰንጠረዥ 2/2 የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮች**

| የቤት ቁሣቁስ | የቤት ቁሣቁስ ለመሥራት የሚያገለግሉ ነገሮች |
|---|---|
| ብረት ድስት | |
| ሸክላ ድስት | |
| ጆንያ | |
| ፍራሽ | |
| መጥበሻ | |
| ጠረጴዛ | |
| ወንበር | |
| ቢላዋ | |

**መልመጃ** 2.13

ተማሪዎች! የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች ከምን ከምን የተሠሩ ይመስላችኋል?

የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከመስታወት ከሸክላ ወይም ከፕላስቲክ ሊሠሩ ይችላሉ፡፡






*ሥዕል 2.17 የቤት ዕቃዎችን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ነገሮች*

ተማሪዎች! አሁን ደግሞ የቤት ውስጥ እቃዎችን ለመሥራት የሚያገለግሉ ቁሣቁሶችን እናያለን። የቤት ውስጥ ቁሣቁሶችን ከዚህ በፊት ተምራችኃል።

## የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ለመሥራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች

ተማሪዎች! በመኖሪያ ቤታችሁ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ በርካታ ቁሳቁሶች አሉ፡፡ ለምሳሌ መቀስ፣ መርፌ፣ መዶሻ፣ መፍቻ፣ ጠመንጃ መፍቻዎች፣ መጥረቢያ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ተማሪዎች! ሌሎች ያልተጠቀሱ የተለያዩ ተግባራትን ለመሥራት የሚያገለግሉ የቤት ቁሣቁሶችን ዘርዝሩ፡፡



ሥዕል 2.18 *የተለያዩ ሥራዎች ለመሥራት የሚያገለግሉ የቤት ቁሣቁሶች*

## 2.3.4 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሣቁሶችን በጥንቃቄና በንፅህና መጠቀም

መልመጃ 2.14

ተማሪዎች! የቤት ዕቃዎችን ወይም ቁሣቁሶችን በጥንቃቄ ያለመጠቀም ምን ችግር ያመጣብናል?

የቤት ዕቃዎችን ወይም ቁሣቁሶችን በጥንቃቄ ባለመጠቀም የእጅ መቆረጥ፣ መወጋት፣ የኤሌክትሪክ ንዝረት፣ የአይን መጎዳትና ሌሎች የአካል ጉዳቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶችን በጥንቃቄ መጠቀም ይገባናል፡፡ እስቲ ተማሪዎች! ወላጆቻችሁ የቤት ውስጥ ቁሣቁሶች አደጋ እንዳያስከትሉ የሚያደርጓቸውን ጥንቃቄዎች ለመምህራችሁ አንድ በአንድ ንገሯቸው፡፡



*ሥዕል* 2.19 *የቤት ውስጥ ቁሣቁሶችን በንፅህና በጥንቃቄ በመያዝ በተገቢ ቦታ ማስቀመጥ*

## የቤት ውስጥ ቁሣቁሶችን ከተጠቀምንባቸው በኋላ ምን ማድረግ አለብን?

# ምዕራፍ ሶስት

# ትምህርት ቤታችን

## 3.1. የትምህርት ቤታችን ግቢ

### 3.1.1. የትምህርት ቤታችን አንፃራዊ መገኛ

የአቅጣጫ ማመልከቻዎች፡- ቀኝ፣ ግራ፣ ፊትና ኋላ ናቸው



*ሥዕል* 3.1 *አቅጣጫን ማመልከት*

| |
|---|
| መልመጃ 3.1<br><br>በሁለት እግራችሁ ቀጥ ብላችሁ ከቆማችሁ በኋላ ፊት፣ ኋላ፣ ቀኝና ግራችሁን አመልክቱ፡፡ |





*ሥዕል* 3.2 *የትምህርት ቤት መገኛ አቅጣጫ*

**መልመጃ 3.2**

1. ከላይ በሥዕሉ ላይ እንደተመለከተው ትምህርት ቤቱ ከፓሊስ ጣቢያው በስተየት ይገኛል?
2. ትምህርት ቤቱ ከፍርድ ቤቱ በስተየት ይገኛል?
3. ትምህርት ቤቱ ከክሊኒኩ በስተየት ይገኛል?

## የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም



*ሥዕል* 3.3 *መፀዳጃ ቤቶች*

**መልመጃ 3.3**

1. በትምህርት ቤታችሁ ያለው መፀዳጃ ቤት ለምን አገልግሎት ይውላል?
2. በትምህርት ቤታችሁ ያሉትን መፀዳጃ ቤቶች እንዴት ትጠቀሙባቸዋላችሁ?

**የእጅ ንፅህና አጠባበቅ**

እጆቻችንን በአራት ወሳኝ ጊዜያት ማለትም ከመጸዳጃ ቤት መልስ፣ምግብ ከማዘጋጀት በፊት፣ ከመመገብ በፊትና በኂላ እንዲሁም ህጻናትን ካፀዳዱ በኂላ መታጠብ ያስፈልጋል ፡፡



*ሥዕል 3.4 እጅን መታጠብ*

| መልመጃ 3.4 |
|---|
| 1. እጆቻችንን መታጠብ ያለብን መቼ ነው? |
| 2. መጸዳጃ ቤት ከተፀዳዳን በኂላ እጆቻችንን ባንታጠብ ምን እንሆናለን? |

## 3.1.2. የትምህርት ቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎች

ከጓደኛ ጋር መጫወት





ከጓደኞች ጋር አብሮ መወያየት


*ሥዕል* 3.5 *የተለመዱ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች*

**መልመጃ 3.5**


1. ጓደኞቻችሁ እነማን ናቸው?
2. ከጓደኞቻችሁ ጋር ምን ምን ጨዋታ ትጫወታላችሁ?
3. ከጓደኞቻችሁ ጋር ምን ምን ስራዎችን ትሰራላችሁ?

## 3.2 ደንብና ስነ-ስርዓት ማክበር

የትምህርት ቤት ደንብና ስነ-ስርዓት








*ሥዕል* 3.6 *ደንብና ስርአት አክባሪ ተማሪዎች*

መልመጃ 3.6

1. የትምህርት ቤታችሁ ህጎችና ደንቦች ምን ምን ናቸው?
2. ትምህርት ቤታችሁ ህግና ደንብ ለምን ያስፈልገዋል?
3. በእናንተ ክፍል ውስጥ መምህራችሁ ጥያቄ ሲጠይቋችሁ መልስ የምትመልሱት በምን መልክ ነው?
4. በክፍል ውስጥ ሆናችሁ መምህር ወይም ሌላ ሰው ከውጪ ሲገባ ምን ታደርጋላችሁ? ይህን ለምን ታደርጋላችሁ?

## 3.3 መልካም ግንኙነትን መመስረት

መልካም ግንኙነት በትምህርት ቤት፣ በአካባቢና በጐረቤት መመስረት ያስፈልጋል፡፡



*ሥዕል 3.7 የትምህርት ቤት መልካም ግንኙነት*



ሥዕል 3.8 የቤትና የጎረቤት መልካም ግንኙነት

**መልመጃ 3.7**


1. ከላይ በሥዕል 3.8 ላይ የምታዩዋቸው ልጆች ምን እያደረጉ ነው?
2. እናንተ ጓደኞቻችሁን በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ አካባቢያችሁ ስታገኟቸው ምን ታደርጋላችሁ?
3. መምህራንን በመንገድ ላይ ስታገኟቸው ምን ታደርጋላችሁ?

## 3.4 የመንገድ ላይ ትራፊክ ደህንነት

በመንገድ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች



የመኪና አደጋ



በእንስሳት የሚከሰት አደጋ


*ሥዕል 3.9 የመንገድ ላይ አደጋ*

**መልመጃ 3.8**

1. ከላይ በሥዕል  የተመለከተዉ አደጋ ምንድን ነው? ለምን የተከሰተ ይመስላችኋል?
2. እናንተ ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ ወይም ወደ ቤታችሁ ስትመልሱ የመኪና መንገድ እንዴት ታቋርጣላችሁ?
3. መንገድ ስትቋርጡ እጃችሁን ይዞ የሚያሻግራችሁ ሰው አለን? ካለ ለምን እጃችሁን ይይዛችኋል?
4. ከመኪና አደጋ ውጪ በመንገድ ላይ የሚያጋጥሙ የአደጋ አይነቶች ምን ምን ናቸው?

# የትራፊክ አደጋን መከላከል

## የትራፊክ ህጐችን ማክበር



*ሥዕል* 3.10 *አስተውሎ በእግረኛ መሺጋገሪያ መንገድ ላይ ማቋረጥ*




*ሥዕል* 3.11 *የመንገድን ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ*

| |
|---|
| መልመጃ 3.9 |
| 1. እግረኛ መንገደኞች ግራቸውን ይዘው የሚሄዱትና ሲያቋርጡም በእግረኛ ማቋረጫ መንገድ የሚጠቀሙት ለምን ይመስላችኋል? |
| 2. ግራቸውን ይዘው የማይሄዱ ሰዎች ምን ይገጥማቸዋል? |

## 3.5. በትምህርት ቤታችን ውስጥ ከወረቀት የምንሰራቸው መጫወቻዎች

ከወረቀት ፉራፉሪትን ለመስራትና ለመጫወት የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች በመከተል ስሩ።




*ሥዕል* 3.12 *የፉራፉሪት አሰራር ቅደም ተከተል*

ተማሪዎች! እናንተም ከወረቀት ፉራፉሪትና ሌሎች ቅርፃ ቅርፃችን በመስራት ተጫወቱ።

# ምዕራፍ አራት


# አካባቢያችንና ቀበሌያችን

## 4.1. አቅጣጫን ማወቅ

### ሀ. ፊት ለፊት ፣ኋላ፣ ግራና ቀኝ

ፊት ለፊት - ውሻው ከድመቷ ፊት ለፊት ይገኛል፡፡





ድመት

ውሻ

ዛፉ ከቤቱ ኋላ ይገኛል፡፡



ሥዕል 4.1 ፊትና ኋላ

**ግራና ቀኝ**

**ግራ**



**አባት** **ልጅ**

**ልጁ ከአባቱ በግራ በኩል ተቀምጧል፡፡**

**ቀኝ**



**ህፃኑ ከእናቱ በቀኝ በኩል ይገኛል፡፡**

ሥዕል 4.2 ግራና ቀኝ

**መልመጃ 4.1**

1. ከእናንተ መቀመጫ ፊት ለፊት ማን ተቀምጧል?
2. ከእናንተ መቀመጫ ኋላ ማን ተቀምጧል?
3. ከእናንተ መቀመጫ በግራ በኩል ማን ተቀምጧል?
4. ከእናንተ መቀመጫ በስተቀኝ በኩል ማን ተቀምጧል?

## ለ. የትምህርት ቤት አካባቢ መገኛን ማስተዋል


**በትምህርት ቤታችሁ ውስጥና ዙሪያ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ?**

መንደር 1



መንደር 2






*ሥዕል* 4.3 *መገኛ ቦታ*

| |
|---|
| *መልመጃ* 4.2 |
| 1. ትምህርት ቤቱ  ከዛፉ በየት በኩል ይገኛል? |
| 2. ከትምህርት ቤቱ በሰተጀርባ በኩል ምን አለ? |
| 3. ከመንደር አንድ በግራ በኩል  ምን አለ? |
| 4. የምትኖሩበትን ሰፈር አቅጣጫና መገኛ ተናገሩ፡፡ |

**ጨዋታ፡- ተማሪዎች! ከክፍል ውጪ በመውጣት በስዕሉ መሠረት ተጫወቱ፡፡**



*ሥዕል* 4.4 *ጨዋታ*

**ተማሪዎች! ከክፍል ውጭ ውጡና ክብ ሰርታችሁ ከመካከለችሁ አንድ ተማሪ  ፊቱን ይሸፈንና  ከክቡ መሃል ገብቶ ይቁም፡፡ ከዚያም በግራዬ**

ማን ነው? በቀኝ ማን ነው? ፊት ለፊት ማን ነው? በኋላየሰ? ማነው እያለ ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች ሲመልሱ ከተሳሳቱት መሀል እየገቡ ይቀመጣሉ፡፡

## 4.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት የሌላቸው ነገሮች

በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም ሕይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸው በመባል ይታወቃሉ።

**መልመጃ 4.3**

ከዚህ በታች ያሉትን ስዕሎች በማየት ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው በማለት ለዩ ።



*ሥዕል* 4.5 *ህይወት ያላቸውና ህይወት የሌላቸው ነገሮች*

### 4.2.1 አየር

**የአየር መኖርን ማረጋገጥ**

አየር በአካባቢያችን ከሚገኙና ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች እንዱ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡




ሥዕል 4.6 *በፊሳሽ ውስጥ አየር መኖሩን ማረጋገጥ፡፡*

## የአየር ጠቀሜታ

በሥዕሉ መሰረት የሚከተለውን ሙከራ ስሩ

**መልመጃ** 4.4


1. በሚበራ ሻማ ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው ብርጭቆ ሙሉ በሙሉ በሚደፋበት ጊዜ የትኛው ሻማ መጀመሪያ ጠፋ? ለምን?
2. አፋችሁን በመዝጋት አፍንጫችሁን ለትንሽ ሴኮንድ በሁለት ጣታችሁ በመያዝ የተሰማችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



*ሥዕል* 4.7 *የአየር ጠቀሜታ*

## 4.2.2 ውሃ

ውሃ ከየት  ይገኛል?



ሥዕል 4.8 የውሃ መገኛዎች

ውኃ ከቧንቧ፤ ከምንጭ፣ ከዝናብ፣ ከወንዝና ከጉድጓድ ወይም ከኩሬ ይገኛል፡፡

## ውሃና ጥቅሞቹ


**መልመጃ 4.5**


1. ውሃ ለምን ያስፈልገናል? ያለ ውሃ መኖር ይቻላልን? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ውሃን በመኖሪያ አካባቢያችሁን እና በትምህርት ቤታችሁ ለምን ትጠቀሙበታላችሁ?











ሥዕል 4.9 የውሃ ጠቀሜታዎች


ውሃ ህይወት ላላቸው ነገሮች ማለትም ለእንስሳትና ለተክሎች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ተክሎች ውሃን ከመሬት ውስጥ በስሮቻቸው አማካኝነት ይስባሉ፡፡ ሰውና አንስሳት ውሃን ይጠጣሉ፡፡ንፅሕናቸውን ለመጠበቅ ይጠቀሙበታል፡፡


### 4.2.3. አፈር

**መልመጃ** 4.6

1. በአካባቢያችሁ ያሉ ተክሎች የሚያድጉት በምን ላይ ነው?
2. በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ የእርሻ ቦታ ሂዱና የበቀሉ አዝርዕቶችን በመመልከት አፈር ለተክሎች የሚሰጠውን ጥቅም ተናገሩ ፡፡
3. በአካባቢያችሁ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች አፈርን ለምን ለምን ጥቅም ያውሉታል?

በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ በእርሻ የሚተዳደር ቤተሰብ በመሄድ አፈር ለእርሻ ሥራ ለምን እንደሚያስፈልግ በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው ፡፡





*ሥዕል 4.10 የአፈር ጥቅም*

## 4.3. በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች

**መልመጃ 4.7**


በአካባቢያችሁ ህይወት ያላቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

### 4.3.1. ተክሎች

ሀ. የተክሎች ሥም

**መልመጃ 4.8**


በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተክሎችን ዓይነት ስም ተናገሩ፡፡











ሥዕል 4.11 በአካባቢያችን የሚገኙ ተክሎች

## ለ. ተክሎችን መመደብ

**መልመጃ 4.9**

1. በምትማሩበት ትምህርት ቤት ወይም በአካባቢያችሁ በመዘዋወር ያያችሁትን ተክሎቸ ስም ተናገሩ፡፡
2. በምትማሩበት ትምህርት ቤት ወይም በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተለያዩ ተክሎችን ናሙና ሰብስቡ፡፡
3. የሰበሰባችኋቸውን ተክሎች ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎች እና ትንንሽ ተክሎች በማለት መድቡ፡፡

## ሠንጠረዥ 4/1፡- የተለያዩ ተክሎችን መመደብ

| ትንንሽ ተክሎች | ቁጥቋጦዎች | ዛፎች |
|---|---|---|
| | | ባህር ዛፍ |
| | | |
| | | |
| | | |

## ሐ. የተክሎች ጥቅም

**መልመጃ** 4.10

በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ሰዎች ተክሎችን ለምን ለምን ይጠቀሙባቸዋል?

ተክሎች ለምግብነት ያገለግላሉ፡፡

**መልመጃ** 4.11

1. በቤታችሁ ለምግብነት የሚያገለግሉ ተክሎችን ስም ተናገሩ ፡፡
2. በቤታችሁ ከምትመገቧቸው ምግቦች ውስጥ ከተክሎች የሚገኙትን ተናገሩ፡፡



*ሥዕል 4.12 ከተክሎች የሚገኙ ምግቦች*


ተክሎች ለሰው እና ለእንስሳት ቤት መስሪያነት ያገለግላሉ፡፡

**መልመጃ 4.12**

እናንተ ባላችሁበት አካባቢ ቤተሰቦቻችሁ ወይም የአካባቢያችሁ ሰዎች ቤታቸውን የሚሠሩት ከምንድን ነው?








*ሥዕል* 4.13 *ከተክሎች የተሠሩ ቤቶች*


**ተክሎች የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን ለመስራት ያገለግላሉ፡፡**

**መልመጃ 4.13**

በቤታችሁ ከሚገኙ የቤት ዕቃዎች ውስጥ ከዕፅዋት የተሰሩትን ሥም ጥሩ፡፡







**ሥዕል 4.14** *ከተክሎች የተሰሩ የቤት ዕቃዎች*


ተክሎች ለማገዶነት ያገለግላሉ



ሥዕል 4.15 *ተክሎች ለማገዶነት ያገለግላሉ*

## በደኖች ውስጥና በዛፎች ላይ የሚኖሩ እንስሣት

ተክሎች ለዱር እንስሳት መጠለያነት ያገለግላሉ፡፡



ሥዕል 4.16 *በዛፎች ውስጥና በዛፎች ላይ የሚኖሩ እንስሣት*

**መልመጃ 4.14**

1. በአካባቢያችሁ ደን ወይም ዛፎች አሉን?
2. በደኑ ውስጥ እና በዛፎቹ ላይ ምን ምን እንስሳት ይኖራሉ?



*ሥዕል* 4.17 *ተክሎች የአፈር መሸርሸርን ይከላከላሉ*

ተክሎች አካባቢን ለማስዋብ ይጠቅማሉ፡፡



*ሥዕል* 4.18 *በተክሎች የተዋበ አካባቢ*

## መ. የተክሎች እንክብካቤ

**መልመጃ** 4.15.

ተክሎች ጉዳት ሳይደርስባቸው እንዲያድጉ ምን መደረግ አለበት?



*ሥዕል* 4.19 *ተክሎችን መንከባከብ*

## 4.3.2. እንስሳት


### ሀ. በአካባቢያችን የሚገኙ እንስሳት


*መልመጃ* 4.16.

በአካባቢያችሁ ወይም በቤታችሁ የሚገኙ የእንስሳትን ስም ተናገሩ፡፡























ሥዕል 4.20 በአካባቢያችን የሚገኙ እንስሳት

## ለ. እንስሳትን መመደብ

**መልመጃ** 4.17

ከአሁን በፊት የምታውቋቸውን እና ከላይ በስዕል የተመለከታችኋቸውን እንስሳት ለማዳና ለማዳ ያልሆኑ በማለት በሰንጠረዡ ውስጥ መድቧቸው፡፡

ሠንጠረዥ 4/2 እንስሳትን መመደብ

| የቤት እንስሳት /ለማዳ እንስሳት/ | የዱር እንሰሳት /ለማዳ ያልሆኑእንሰሳት/ |
|---|---|
| ምሳሌ፡- ዶሮ | ምሳሌ፡- ጅብ |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ሐ. የእንስሳት ባህሪያት

**መልመጃ** 4.18.

እንስሳት ምን ምን ባህሪያት አላቸው?


እንስሳት ይመገባሉ፡፡

**መልመጃ** 4.19.

ቀጥሎ ያሉት እንስሳት ምን እየተመገቡ እንደሆነ ለዩ፡፡









*ሥዕል* 4.21 *የእንስሳት አመጋገብ*

**እንስሳት ከቦታ ቦታ ይንቀሣቀሣሉ፡፡**


**መልመጃ 4.20.**

1. እንስሳት ከቦታ ቦታ እንዴት ይንቀሣቀሳሉ?
2. የሚከተሉትን ስዕሎች ተመልክታችሁ እንስሳቱ እንዴት እንደሚንቀሣቀሱ ተናገሩ፡፡




*ሥዕል* 4.22 *የእንስሳት እንቅስቃሴ*

እንስሳት ይራባሉ፡



እንስሳት ያድጋሉ



*ሥዕል* 4.23 *የእንስሣት አረባብና አስተዳደግ*

## መ. የእንስሳት ጥቅም

**መልመጃ** 4.21.

በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ ያሉ እንስሳት ለምን ለምን ይጠቅማሉ?

ለምግብነት

**መልመጃ** 4. 22

የሚከተሉት የምግብ ዓይነቶች ከምን ከምን እንደሚገኙ ተናገሩ?


ሀ. ሥጋ ለ. እንቁላል ሐ. ወተት መ. ዓይብ ሠ. ቅቤ

ለጉልበት ሥራ


**መልመጃ** 4.23

1. ለእርሻ ሥራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ስም ጥሩ፡፡
2. እቃ እና ሰውን ለማጓጓዝ የሚረዱ እንስሳትን ዘርዝሩ፡፡










*ሥዕል 4.24 ለጉልበት ስራ የሚያገለግሉ እንስሳት*

## ለልብስነት እና ሌሎች የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሣቁሶች

**መልመጃ 4.24**

1. ከእንስሳት ቆዳ የተሠሩ ልብሶችን ታውቃላችሁ?
2. በቤታችሁ ውስጥ ከእንስሳት ውጤት የተሠሩ ቁሣቁሶችን ተናገሩ፡፡









*ሥዕል* 4.25 *ከእንስሣት ውጤቶች የተሰሩ አልባሣት*


## ሠ. የእንስሳት እንክብካቤ

**መልመጃ 4.25.**

1. በቤታችሁ ውስጥ እንክብካቤ የሚደረግላቸው እንስሳት አሉን?
2. በቤታችሁ ውስጥ ለትንንሽ እንስሳት እንክብካቤ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት ትንከባከባላችሁ?
3. ለእንስሳት እንክብካቤ ባናደርግላቸው ምን ይሆናሉ?









ሥዕል 4.26 እንስሳትን መንከባከብ

## 4.4. በአካባቢያችን የተለመዱ የሥራ አይነቶች

### 4.4.1 የሥራ ጥቅም





ሥዕል 4 .27 የሥራ ጥቅም

**መልመጃ 4.26**

1. ከሥዕሉ ምን ተማራችሁ?
2. ወላጆቻችሁ ሥራ ባይሰሩ ኖሮ ምን ትሆኑ ነበር?
3. በቤታችሁ ውስጥ በሥራ የተገኙ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡

## 4.4.2 የሥራ ዓይነቶች



*ሥዕል* 4.28 *የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች*

**መልመጃ 4.27**

1. የቤተሰባችሁ አባላት ምን ምን የስራ ዓይነቶች ያከናውናሉ?
2. በሥዕሉ ያስተዋላችኋቸው የሥራ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
3. በመንደራችሁ ያሉ ሰዎች የሚሰሯቸውን ሥራዎች ተናገሩ፡፡

### 4.4.3 በስራ መርካት

**እናንተ ህፃናት ምን ስትሰሩ ደስ ይላችኋል?**

**በስራችን ውጤት  ደስተኞች እንሆናለን፡፡**



*ሥዕል* 4.29 *በሥራ መርካትና መደሰት*

**መልመጃ 4.28**


1. የምታውቋቸውን የሥራ ዓይነቶች ዘርዝሩ? የትኞቹ ስራዎች የበለጠ ያስደስቷችኋል?
2. ሥራ የማይሰሩ ሰዎች ደስ የሚላቸው ይመስላችኋል? ለምን?


ሥራ አዕምሯችንና ጉልበታችንን ተጠቅመን የምናከናውነው ተግባር ነው፡፡ ለሰው ልጆች ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሥራ ስንሰራ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ እናገኛለን፡፡ ካልሰራን ምግብ አናገኝም፡፡ ካለምግብ ደግሞ መኖር አንችልም፡፡ ስለዚህ ምግብ ለማግኘት መሥራት አለብን፡፡

ካልሰራን ልብስ አናገኝም፡፡ ካለበስን ደግሞ ፀሐይና ብርድ ይጐዳናል፡፡ ስለዚህ ልብስ ለማግኘት መሥራት አለብን፡፡ ካልሰራን ቤት አይኖረንም፡፡ ካለመጠለያ ደግሞ ምግብ ማዘጋጀት፣ መተኛት እና ከፀሐይና ከብርድ ራሳችንን መከላከል አንችልም፡፡ ስለዚህ ለመኖር መሥራት አለብን፡፡ በተጨማሪም ካልሰራን ወላጆቻችንን መርዳት አንችልም፡፡ ወላጆቻችንን ካልረዳን ደግሞ ደስ አይለንም፡፡ ስለዚህ ደስ እንዲለን መሥራት አለብን፡፡

## 4.5. የአካባቢያችን መጓጓዣ

### 4.5.1 የመጓጓዣ ምንነትና ጥቅም





ሥዕል 4.30 የመጓጓዣ ጥቅም


**መልመጃ 4.29**

1. ተማሪዎች መጓጓዣ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ተማሪዎች መጓጓዣ ለምን ለምን ይጠቅማል?
3. በአካባቢያችሁ ሰዎች መጓጓዣን ምን ምን ነገሮችን ለማጓጓዝ ይጠቀማሉ?
4. እናንተ በበቅሎ፣ በፈረስና በመኪና ሄዳችሁ ታውቃላችሁ?


መጓጓዣ ሰዎችንና ልዩ ልዩ ነገሮችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚያገለግል ነው፡፡ መጓጓዣ እህልን፣ ሸቀጥን፣ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማንቀሣቀስ ይጠቅማል፡፡ ለምሳሌ ከእርሻ ቦታ ወደ ቤትና ወደ ገበያ እና ከገጠር ወደ ከተማ የግብርና ምርቶችን፣ እንዲሁም ከከተማ ወደ ገጠር የፋብሪካ ውጤቶችንና ሰዎችን ለማጓጓዝ ያገለግላሉ፡፡

## 4.5.2 የመጓጓዣ ዓይነቶች

### ሀ. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች



አህያ



ግመል



ጋሪ


*ሥዕል 4.31 ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች*

ባህላዊ መጓጓዣ ማለት የሰውንና የእንስሳትን ጉልበት በመጠቀም ሰውንና እቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሣቀስ የምንጠቀምበት የመጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በቅሎ፣ ፈረስ፣ አህያና ግመል ሰውንና እቃን ከቦታ ቦታ ያጓጉዛሉ፡፡


## ለ. ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች




አውሮፕላን



መኪና



መርከብ



ባቡር

*ሥዕል 4.32 ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች*

**መልመጃ 4.30**

1. የትኞቹ የመጓጓዣ ዓይነቶች በአብዛኛው ዕቃዎችን ያመላልሳሉ?
2. የትኞቹ የመጓጓዣ ዓይነቶች በአብዛኛው ሰዎችን ያጓጉዛሉ?

ዘመናዊ መጓጓዣዎች ሰውንና ዕቃን በፈጣን ሁኔታ ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ይጠቅማሉ፡፡ መኪና፣ ባቡር፣ መርከብና አውሮፕላን ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ናቸው፡፡ መርከብ ብዙ ዕቃ በአንድ ጊዜ ያጓጉዛል፡፡ ባቡር ብዙ ሰዎችንና ዕቃዎችን ከቦታ ቦታ ያጓጉዛል፡፡ አውሮፕላን ከሁሉም መጓጓዣዎች ፈጣን ነው፡፡

**መልመጃ** 4.31

ቀጥሎ የቀረቡትን የመጓጓዣ ዓይነቶች በምን ላይ እንደሚጓዙ አዘምዱ፡፡

| **የመጓጓዣ ዓይነት** | **የሚጓዝበት** |
|---|---|
| መኪና | በአየር ላይ |
| መርከብ | በሀዲድ ላይ |
| አውሮፕላን | በባህር ላይ |
| ባቡር | በመንገድ ላይ |

1. መኪና በ____________ ላይ ይጓዛል፡፡
2. መርከብ በ___________ ላይ ይጓዛል፡፡
3. አውሮፕላን በ________________ላይ ይጓዛል፡፡
4. ባቡር  በ____________________ላይ ይጓዛል፡፡